Arlington Public Schools

Facilities & Operations, Risk Management
2770 South Taylor Street
Arlington, VA 22206
703-228-6600

ውድ ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ፣

የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከሁሉም ወላጆቻችንና ህጋዊ አሳዳጊዎቻች ጋር ያለንን ግንኙነት ትልቅ ዋጋ ይሰጡታል፡፡ በ APS እና በእናንተ መካከል እንደ ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ ያለው ግንኙነት ተማሪዎ ትምህርት ቤት እያለ ወይም በትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ ሲያደርግ ሊከሰት ከሚችለው አደጋ ጋር በተያያዘ ነገርን መገረጋገጥ የሚከተለውን መረጃ ማንበቡ አስፈላጊ ነው፡፡

APS ለተማሪዎ(ዎችዎ) በትምህርት ቀን ወይም በትምህርት ቤት በሚደገፉ ተግባራት ላይ በሚሳተፉበት ጊዜ ከጉዳት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የህክምና ወጪ ለመሸፈን የአደጋ መድን ሽፋን የሚሰጥ አይሆንም፡፡ ሁሉም ወላጆችና ህጋዊ አሳዳጊዎች በአማራጭ የተማሪ አደጋ መድን ሽፋን ፕሮግራማችን ውስጥ መሳተፍን እንዲያስቡበት አበክረን እናሳስባለን፡፡ ይህ ፕሮግራም የጤና መድን ለሌላቸው ተማሪዎች ብቻ ያይደለ ሲሆን የአማራጭ የተማሪ አደጋ መድን አስቀድሞ በወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና መድን እቅድ ስር ሽፋን ላገኙ ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ ሽፋን ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ነው፡፡ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የአማራጭ የተማሪ አደጋ የመድህን ሽፋን በዋና የመድህን እቅድ ያልተከፈሉ እንደ የጋራ ክፍያና ሌሎች ከኪስ የሚደረጉ ወጪዎችን ሊሸፍን ይችላል፡፡

በአርሊንግተን ካውንቲ ውስጥ ያሉ ሁሉም ቤተሰቦች እንዲሳተፉ በእጅጉ እናበረታታለን፡፡ በዘንድሮው አመት መርሃ ግብር ለአንድ ተማሪ በመረጡት ሽፋን ላይ በመመርኮዝ ለጠቅላላው የትምህርት ዘመን ከ $9 እስከ 154 ዶላር መካከል ያለውን የቡድን ዋጋ ይሰጣል፡፡ ወላጆች በመስመር መቀበያው (ኦንላይን ፖርታል) ወይም ከታች በተጠቀሰው ቁጥር ለ Young Group, Inc. በመደወል ተማሪዎችን ማስመዝገብ ይችላሉ፡፡ ወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች አሁን ከኦገስት 28/2023 ጀምሮ እስከ ሰኔ 14/2024 ድረስ ተማሪዎቻቸውን ለፖሊሲ ሽፋን ማስመዝገብ ይችላሉ፡፡

ለበለጠ መረጃ ወይም በ Young Group, Inc. በቀረበው እቅድ ለመመዝገብ በ 1-888-574-6288 ወይም 1-919-9798 ይደውሉ ወይም https://www.k12studentinsurance.com ይጎብኙ፡፡

ተማሪዎች ህመም ወይም ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ የህክምና መድን ሽፋን ከሌላቸው፣ ሽፋኑ ለቤተሰብ በህክምና መድን ዋስትና (FAMIS) ፕሮግራም በኩል ይገኛል፡፡ FAMIS የተወሰኑ ገቢዎችንና ሌሎች የብቃት መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ቤተሰቦች ይገኛል፡፡ ፕሮግራሙ በቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ ስፖንሰር የተደረገ ነው፡፡ ስለ FAMIS መረጃና የምዝገባ ቅጾች በመስመር http://www.coverva.org/main_apply.cfm ላይ ወይም በ 1-855-242-8282 በመደወል ማግኘት ይቻላል፡፡

ከሰላምታ ጋር፣

አምበር ዴቪስ
ተጠባባቂ ስጋት ኃላፊ፣ ማመቻቸትና ስራዎች

//en//